በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

**ጠ/ሚር ጽቤት ርዕሰ አንቀጽ**
**ሚያዚያ 2013**

## ኢትዮጵያ እና ዜጎቿ ሰላማዊ እና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ለማካሄድ ታይቶ የማይታወቅ ዕድል ተመቻችቶላቸዋል።

ኢትዮጵያ በፖለቲካ ታሪኳ አንድ ወሳኝ የለውጥ ወቅት ላይ ትገኛለች። በረጅሙ የሀገረ መንግሥት እድሜዋ ታይቶ የማይታወቅ የፖለቲካ ለውጥ እየተደረገ ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ የሕዝብ ፣ ለሕዝብ እና በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት ለማቋቋም በእውነተኛ ሂደት ላይ እንገኛለን። ሁሉም ባለድርሻ አካላት፤ ሕዝብ ፣ መንግሥት ፣ ፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ሲቪል ማኅበራት እና መገናኛ ብዙኃን በጋራ በገቡት ቁርጠኝነት ወደ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ የሚደረግ ጉዞ ተጀምሯል።

እንደ እኛ ላሉት አዳጊ ሀገራት፣ ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ ሁላችንም ልንከባከበው እና ልንጠብቀው የሚገባ ብርቅዬና ውድ አጋጣሚ ነው። ከታሪካችን እንደምንማረው ገዥዎቻችን በጭራሽ በዜጎች የተመረጡ ሳይሆን በአፈ ሙዝ ወደ ሥልጣን መጥተው በተመሳሳይ እስኪወገዱ በመሣሪያ የሚገዙ ነበሩ። የግንቦት 2013ቱ ሀገራዊ ምርጫ ለሁላችን ይህን መጥፎ አዙሪት እንደሚያስቆም ተስፋ ተጥሎበታል። በልዩ ሁኔታ እና በጥራት ልዩነት ላለው የፖለቲካ ለውጥ ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ ዕድል ይሰጣል። ዓላማውም አዲስ መንገድ፤ በተለይም ዘላቂ መንገድ ማመላከት ነው።

ይህ አስተዳደር ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ኢትዮጵያ ከዚህ በፊት በእርግጥም ተሳክቶላት የማያውቅ - ነጻ እና ፍትሐዊ ምርጫ ለማካሄድ ቅድሚያ ሰጥቶ ሲዘጋጅ ቆይቷል። በተመሳሳይም አስተዳደሩ በኢትዮጵያ ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ እንዲኖር የማያወላውል ቁርጠኝነቱን ደጋግሞ ገልጿል። ነጻ እና ፍትሐዊ ምርጫ - ወደ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር ብቸኛው ሕጋዊ መንገድ - የዴሞክራሲ መሠረት እና መሠረታዊ ጉዳይ ነው። ይህ ምርጫ መንግሥት ባከናወናቸው ጉልህ የፖለቲካና የሕግ ማሻሻያዎች መሠረት የመጣ ነው። በእርግጥም የፖለቲካ ምኅዳሩን ለማስፋት እና ሁሉም ኢትዮጵያውያን በእኩል ዕጣ ፈንታቸውን በፖለቲካ አደረጃጀት፣ በዘር እና በሃይማኖት ማንነት ሳይለዩ በተሟላ ነጻነት እና እኩልነት እንዲቀርጹ ለማስቻል በርካታ ደፋር እና ያልተለመዱ ርምጃዎች ታሳቢዎች ተደርገዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ተፎካካሪ ፓርቲዎችን የገዥው ፓርቲ ተቃዋሚዎች ከማለት ይልቅ አማራጭ ሐሳቦችን ይዘው የቀረቡ ተፎካካሪዎች የሚል ዕውቅና በሰጡበት የሹመት የመክፈቻ ንግግራቸው ሁሉም ፓርቲዎች ገንቢ በሆነ መልኩ የሚንቀሳቀሱበት ፍትሐዊና የተስተካከለ የመጨዋቻ ሜዳ እና ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጠር ቃል ገብተዋል። ይህንንም ተከትሎ የወንጀል ክሶች እና የጥፋተኝነት ፍርድ የነበራቸው የፖለቲካ እስረኞች ከእስር ተፈትተው በስደት ያሉ የፖለቲካ ተቃዋሚዎች ወደ ሀገር ተመልሰዋል። ያንን ለማሳካት ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች እና ተቃዋሚዎች የተቸራቸው ይቅርታና ምሕረት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለጉዳዩ ያላቸውን ቁርጠኝነት የበለጠ የሚያሳይ ነው። እነዚህ ርምጃዎች በእውነተኛ ብሩህ ተስፋ እና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ላይ እምነት እንዲፈጠር አድርጓል። ሆኖም አስፈላጊ የሕግ ማሕቀፍ እና አተገባበሩን ከሚቆጣጠሩ ገለልተኛ ተቋማት ውጭ የትኛውም ምርጫ ነጻ፣ ፍትሐዊ እና ዴሞክራሲያዊ ሊሆን አይችልም። ያለፈው ያልተስተካከለ የመጨዋቻ ሜዳ ክፍተቶች በመረዳት፤ የምርጫ እና የፖለቲካ ፓርቲ ሕጎች ተሻሽለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነጻነቱን በሚያረጋግጥ መልኩ እንዲዋቀር ተደርጓል።

ምርጫ ቦርድ ዛሬ ነጻ እና ፍትሐዊ ምርጫዎችን ለማካሄድ የገንዘብ እና የቴክኒክ ዐቅም እና ተቋማዊ ነጻነት አለው። ቦርዱ የሚመራው በታዋቂዋ የቀድሞ ዳኛ እና የተቃዋሚ ፓርቲ መሪ ሲሆን የሊቀ መንበርነታቸው ሹመት በአጠቃላይ ተቀባይነት አግኝቷል። የምርጫ አስተዳደርን አስመልክቶ የተደረጉት ማሻሻያዎች ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት እና ከምርጫ ሕጉ ጋር የማይጣጣሙ አሠራሮችን አስወግደዋል። ቦርዱ ሁሉንም አካላት ሕግና አሠራርን ብቻ በመከተል እያገለገለ ይገኛል፡፡ ለዚህም የተፎካካሪም ሆነ የገዥ ፓርቲውን ጥያቄዎች የተቀበለውን ያህል የሁለቱንም ጥያቄዎች ያልተቀበለበት ጊዜም አለ፡፡ በዚህም ለሕግ እንጂ ለሌላ ለማንም ያልቆመ መሆኑን አሳይቷል፡፡ በተጨማሪም ፣ ተስማሚ እና የሲቪልና የፖለቲካ ምኅዳሩን ጤናማነት ለማረጋገጥ ቀጥተኛ ተጽዕኖ ያላቸው ሌሎች ሕጎች እንዲሻሻሉ ወይም በአዲስ እንዲለወጡ ተደርጓል። እንደ ምሳሌም በመደበኛነት ተቃዋሚዎችን ወይም ተፎካካሪዎችን ለማፈን ሲያገለግል የቆየው እና አሁን የተሻሻለውን የፀረ ሽብርተኝነት ሕግ እና የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር አዲስ የወጣውን ዐዋጅ መጥቀስ ይቻላል። የሕግና ተቋማዊ ዝግጁነት ብቻ ግን ሁላችንም የምንናፍቀውን ዴሞክራሲያዊ ምርጫ አያስገኝም። ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ማካሄድ የጋራ ኃላፊነትን ይጠይቃል። ሁሉም የምርጫ ተሳታፊዎች በሥራ ላይ ያሉትን ሕጎችና ሥርዓቶች ለማክበር መወሰን አለባቸው። ማናችንም የምርጫውን ታማኝነት እና ተአማኒነት የሚያደናቅፍ ማንኛውም ተግባር ላይ መሳተፍ ወይም መታገስ የለብንም።

መንግሥት ነጻ፣ ፍትሐዊ እና ሰላማዊ ምርጫዎች እንዲካሄዱ እና ዓላማዎቻቸውን እንዲያሳኩ የማድረግ ተቀዳሚ ግዴታ አለበት። ወደ ምርጫ በሚመጣበት ጊዜ ግን ኃላፊነቱ መንግሥት ጋር ብቻ አይቆምም። ሁሉም - ከመንግሥት ባለሥልጣናት እስከ የፖለቲካ ፓርቲዎች አባላት፣ ከምርጫ አካላት፣ ከሕግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች፣ ከፍትሕ አካላት፣ ከሲቪል ማኅበራት እንዲሁም በእርግጥ መራጮች እና አጠቃላይ ዜጎች - ሁሉም የሚጫወቱት ሚና አላቸው። ስለሆነም እያንዳንዱ ሰው ኃላፊነቱን ተረድቶ እንዲወጣ ማድረጉ ወሳኝ ነው። የፖለቲካ ፓርቲዎች በፓርቲዎች የሚደገፉ አካሄዶችም ሆኑ የአባላት ወይም የደጋፊዎች ተግባር፤ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ሕገ ወጥ ድርጊቶችን ሁሉ መሰረዝ አለባቸው። የሕዝብን አስተያየት እና አቋም እንደሚቀርፁ መረዳት አለባቸው። ሕገ ወጥ ድርጊቶች የምርጫ ሂደቶችን እና ውጤቶችን ተአማኒነት የሚሸረሽሩ፣ በድሉ ትክክለኛነት ላይ ጥርጣሬ የሚፈጥሩ እና በመጨረሻም ወደ ግጭቶች ሊያመሩ ይችላሉ። የፖለቲካ ፓርቲዎች በትኩረት እና ትርጉም የሚሰጡ ሐሳቦች መመራት፣ በሲቪል መግባባት እና የንትርክ ንግግርን ማስወገድ አለባቸው።

የምርጫ አስፈጻሚዎች ኃላፊነታቸውን በሕጉ መሠረት በጥብቅ ማከናወን አለባቸው። የፈጸሙት ወይም የዘነጉት ዴሞክራሲን ሊያቅፍ ወይም ሊያደናቅፈው እንደሚችል ሁል ጊዜም ልብ ሊሉት ይገባል። ሥራቸውን በሚሠሩበት ጊዜ ሊያጋጥሟቸው ከሚችሏቸው ማናቸውም ችግሮች ጋር መጽናት አለባቸው። የሕግ አስከባሪ አካላት ዲሞክራሲያዊ ምርጫን በማካሄድ ረገድ የፖሊስ ጥበቃና ደኅንነትን በማስጠበቅ ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ መሆኑን አምነው መቀበል አለባቸው፡፡ ስለሆነም ግዴታቸው በሕጋዊ መንገድ የሚከናወን ከመሆኑም በላይ ሁሉንም በእኩልነት እና በገለልተኝነት ያስተናግዳሉ። የፍትሕ አካላት ከምርጫዎቹ ጋር ተያይዘው ሊነሡ የሚችሉ በሥርዓቱ ውስጥ ያሉ ጉዳዮችን ሁሉ በአግባቡ እና በፍጥነት ለማስተናገድ እና ሁሉንም በእኩል እና በገለልተኝነት ሊያዩ መዘጋጀት አለባቸው።

ገለልተኛ፣ ብቁ ፣ ሞያተኛ እና ነጻ መገናኛ ብዙኃን ሚና ከሌሎቹ ባልተናነሰ አስፈላጊ ነው፡፡ ከስሜታዊነት ነጻ የሆነ፣ እውነትን የሚፈልግ፣ በኅብረተሰባችን ውስጥ ሰላምና ዕርቅ እንዲኖር የሚሠራ፣ ዜጎችን ለማስተማር የሚውል ሚዲያ ያስፈልገናል፡፡ ይህ ሚዲያ በሥልጣን ላይ ያሉትን ከሕግ ውጭ እንዳይሄዱ የሚገዳደራቸው ሊሆን ይገባል። ዜጎች በመረጧቸው የፖለቲካ እና ሲቪክ አደረጃጀቶች አማካይነት በሀገራቸው አስተዳደር ውስጥ ንቁና ገንቢ ተሳትፎ ማድረጋቸው ወሳኝ መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል። ዴሞክራሲያዊ ሀገር መገንባት የሁሉንም ተሳትፎ የሚጠይቅ መሆኑን እና ምርጫዎች የዴሞክራሲ መሠረት መሆናቸውን ለመምረጥ ብቁ የሆነ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሊገነዘበው ይገባል። ስለሆነም በምርጫዎቹ ላይ መመዝገብ እና ድምፅ መስጠት ይኖርባቸዋል። መራጮች እና ሌሎች ዜጎች የምርጫውን ታማኝነት ለማረጋገጥ ከእነርሱ የሚጠበቀውን ማድረግ እና ሊከሡቱ የሚችሉ ጉዳዮችን ለመፍታት በሕጋዊ መንገድ የተቋቋሙ ሥርዓቶችን ማመን አለባቸው። እያንዳንዳችን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮቻችን መፍትሔ ሊያገኙ ይገባል በሚለው ላይ እያንዳንዳችን ከሌላው የተለየ አመለካከት ወይም አቋም ሊኖረን እንደሚችል መቀበል አለብን፡፡ የራሳችን ሐሳቦች ዋጋ ማየት የምንችለው የሌሎችን ሐሳቦች ዋጋ ለመስማት እና በእውነት ለመገምገም በአክብሮት ስንነሣ ብቻ ነው።

በእውነተኛ ዴሞክራሲ ውስጥ ግለሰቦች እና ፓርቲዎች ያሸንፋሉ ወይም ይሸነፋሉ ግን ለአጭር ጊዜ ብቻ። በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ግለሰብ የተወሰነ የምርጫ ውድድር ቢያሸንፍም ቢሸነፍም ሥርዓቱ ሁል ጊዜ ያሸንፋል። ይህ እየተሻሻለ የሚሄድ እና ሁል ጊዜም የሚያብብ ሥርዓት ነው፡፡ እናም ሰላማዊ ሆነው በሕጎች ላይ የተመሠረቱ የሥልጣን ውድድሮች በግለሰቦች እና በቡድኖች መካከል ጠንካራ የዴሞክራሲ መሠረትን ይጥላሉ። ያለፉትን ስሕተቶች ደግመን ይህን ዕድል አናባክን። ይህ ምርጫ በሀገራችን ረዥም ታሪክ ውስጥ በተሸለ ሁኔታ የሐሳብ ብዝኃነት እና የፖሊሲ አማራጮች የተወከሉበት፤ በነጻነት፣ በእኅትማማችነት እና በወንድማማችነት ለሚያምኑ ሁሉ ቦታ የሚሰጥ፤ የዘር፣ የሃይማኖት ወይም ሌሎች ልዩነቶች ባለፈ፣ የጋራ ደኅንነታችን በእያንዳንዳችን ደኅንነት ላይ የተመሠረተ መሆኑን የሚገነዘብ ምክር ቤት በመመሥረት፣ ለኢትዮጵያ አዲስ ምዕራፍ እንደሚከፍት ጽኑ እምነት አለን።

//